በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# አሠርቱ ትእዛዛት - ክፍል ፩

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

የካቲት ፳፫ ቀን ፳፱፫ ዓ.ም.

# አሠርቱ ትእዛዛት

## *መግቢያ*

- **አሠርቱ ትእዛዛት በሊቀ ነቢያት ሙሴ ዘመን ወይም ከዚያም ቀድሞ ለነበሩት ብቻ ሳይሆን በየዘመናቱ ለሚነሱ የሰው ወገኖች ሁሉ የተሰጡ ሰማይና ምድር እስኪያልፉ (ዕለተ ምጽአት) ተጠብቀው የሚኖሩ ትእዛዛት ናቸው፡፡** "እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።" **እንዳለ** ***ማቴ 5፡18 - 19፡፡***
- **እነዚህ ትእዛዛት በክርስትና ሳይለወጡ ይልቁኑ ሰፍተውና ተብራርተው ጸንተውም ይገኛሉ፡፡** "… ለቀደሙት። አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።…" ***ማቴ 5፡20 — 48፡፡*** "የሥራህን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ ትእዛዝህ ግን እጅግ ሰፊ ነው። አቤቱ፥ ሕግህን እንደ ምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው።" ***መዝ 118 (119)፡96 — 97፡፡***
- **እግዚአብሔር እነዚህን አሥርቱን ትእዛዛት በጣቶቹ በመጀመሪያ ለሙሴ በሰጣቸው ቀጥሎም ለእምነቱ ባለው ቅንዓት ሙሴ በሰበራቸው ምትክ አድርጎ ባዘጋጃቸው በሁለቱ ጽላቶች ላይ በመጻፍ ቀድሞ ለእስራኤል ዘሥጋ በመቀጠልም ለእስራኤል ዘነፍስ ለክርስቲያኖች ሰጥቷል፡፡** ***ዘጸ 20፡1-17፣ ዘዳግ 5፡1-ፍም፡፡***

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት</u>

- አሠርቱ ትእዛዛት በጠቅላላው ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች እንድንረዳ ያደርጉናል፡፡

1. <u>*በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረገ ኪዳን ነው፡፡*</u>
    - አሠርቱ ትእዛዛት በሊቀ ነቢያት ሙሴ ዘመን ወይም ከዚያም ቀድሞ ለነበሩት ብቻ ሳይሆን በየዘመናቱ ለሚነሱ የሰው ወገኖች ሁሉና ዛሬም ለምንገኘው ለክርስቲያኖችም የተሰጡ ሰማይና ምድር እስኪያልፉ (ዕለተ ምጽአት) ተጠብቀው የሚኖሩ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረገ ኪዳን እንዲሁም ለሰውም የተሰጡ ትእዛዛት ናቸው፡፡ "አምላካችን እግዚአብሔር በኮሬብ ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። እግዚአብሔር ዛሬ በዚህ በሕይወት ካለነው ከእኛ ከሁላችን ጋር እንጂ ከአባቶቻችን ጋር ይህችን ቃል ኪዳን አላደረገም።" እንዳለ <u>*ዘዳግ 5፡2-3፡፡*</u>
    - ትእዛዛቱ የተጻፉባቸው ሁለቱ ጽላቶችም "የቃል ኪዳኑ ጽላቶች" <u>*ዘዳግ 9፡11*</u> ሲባሉ መጽሐፉም የቃል ኪዳኑ መጽሐፍ ተብሏል፡፡ <u>*ዘጸ 24፡7፡፡*</u>
    - እነዚህን ትእዛዛት ታላቅነታቸውን እንረዳ ዘንድ በሲና ተራራ ላይ ተራራው እየጤሰ፣ በደመና ተከቦ፣ የመለከትና የእምቢልታ ድምጽ እየተሰማ ለሙሴ ሰጥቶታል፡፡ "ሙሴም፡- እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበር፡፡" እንዳለ <u>*ዕብ 12፡21፣ ዘጸ 19፡16-19፡፡*</u>
    - ይህም ትእዛዛቱ ምን ያህል ታላቅ እንደሆኑና መፈጸምም ግዴታ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡

# አሠርቱ ትእዛዛት

## 2. *የትእዛዛቱ አስፈላጊነት*

- እነዚህ ትእዛዛት በእግዚአብሔር አንደበት የተነገሩና ዘጸ 20፣ በሁለቱ ጽላቶች ላይ በእጆቹ የተጻፉ ዘዳግ 19 መሆናቸው ተፈላጊነታቸውን ከፍ ያደርገዋል።
- ሊቀ ነቢበበት ሙሴም አሥርቱን ትእዛዛት ተቀብሎ ከተራራው ሲወርድ የሚቃጠልና የደኅንነት መሥዋዕት ከአቀረበ በኋላ ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጭቶታል። *ዘዳግ 24:4-8።*
- እነዚህ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ጣቶች ከአንድ ጊዜ በላይ መጻፋቸው አስፈላጊነታቸውን የሚያጎላው ነው። *ዘዳግ 20:2-17፣ ዘዳግ 5:6-21፣ ዘዳግ 10:41፣ ዘጸ 34:1*

## 3. *የትእዛዛቱ ቁጥር አሥር ስለምን ሆነ?*

- በዕብራውያን አሥር ቁጥር የፍጹምነት ምሳሌ ነው። ትእዛዛቱ አሥር ቢሆኑም የሕግጋትና የትእዛዛት ምሳሌ መሆናቸውን ለማመልከት ነው። የአሥር ቁጥርን የፍጹም ነገር ምሳሌነት በጥቂቱ እንመልከት፦
    - የአሥሩ ደናግል ምሳሌ። *ማቴ 25:1-12።* በዚህ ምሳሌ አሥር ቁጥር ጻድቃንንም ኃጥአንንም - መላውን ዓለም ያመለክታል።
    - አሥር ምናን የተሰጣቸው ባሪያዎች ምሳሌ። *ሉቃ 19:13-17።* እነዚህ አሥሩ ባሮች ጌታቸው እስኪመጣ ድረስ ነግደው እንዲያተርፉ ገንዘቡን የሰጣቸውን ጻድቃንና ኃጥአን ይወክላሉ።
    - የጠፋው ድሪም *ሉቃ 15:8*፣ ነቢዩ ዳንኤል "እኛን ባሪያዎችህን አሥር ቀን ያህል ትፈትነን ዘንድ እለምንሃለሁ የምንበላውንም ጥራጥሬ የምንጠጣውንም ውኃ ይስጡን።" *ዳን 1:12* የቁጥሩን የፍጹም ነገር ምሳሌነት ያመለክታል። *ዘፍጥ 31:7፣ ኢዮብ 19:3።* ለአሥር ቁጥር የተነገረው ሁሉ ለብዜቶቹ (መቶ፣ ሺህ፣ …) ይነገራል። *ሉቃ 15:4፣ 1ኛ ቆሮ 14:19።*

# አሠርቱ ትእዛዛት

## 4. ሁለቱ ጽላቶች

- አሠርቱ ትእዛዛት በሁለቱ ጽላቶች ተጽፈው የሚገኙ ትእዛዛት ናቸው፡፡ በአንዱ ጽላት ላይ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግኑኝነት የሚያመለክቱ ሦስት ትእዛዛት በሌላኛው ጽላት ላይ ደግሞ ሰዎች ከሰዎች ጋር እርስ በርስ በሚኖራቸው ግኑኝነት ላይ የታዘዙ ሰባት ትእዛዛት ይገኛሉ፡፡
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንድ ሕግ አዋቂ በሰጠው ምላሽ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፦ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ጸንተዋል።" ያለው ይህንኑ ሊያመለክተን ነው፡፡ *ማቴ 22፡36-40፡፡*

## 5. ሕገ ልቦናን ያስታውሱናል፡፡

- አሠርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ጣቶች ከመጻፋቸው አስቀድሞ በሕገ ልቦና አባቶቻችን ይመሩባቸው እንደነበር ያስታውሱናል፡፡ ለምሰሌ፡-
  - አትግደል፡- መግደል ቀድሞም ቢሆን ኃጢአት እንነበር ቃየል ወንድሙ አቤልን በገደለው ጊዜ በተቀጣው ከባድ ቅጣት ተገልጧል፡፡ *ዘፍጥ 4፡13፡፡*
  - አታመንዝር፡- ጻድቁ ዮሴፍ የጲጥፋራ ሚስት በዝሙት ወጥመድ አስገድዳ በያዘችው ጊዜ "ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው የለም ሚስቱ ስለ ሆንሽ ከአንቺም በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?" ማለቱ በሕገ ልቦና ዘመን የሚታወቅ ሕግ መሆኑን ያመለክታል፡፡
  - አትስረቅ *ዘፍጥ 31፡30-39*፣ አትመኝ *ኢዮ 31፡1*፣ ሰንበትን አክብር ዘጻግ *16፡23-29፣ ዘፍጥ 2፡2-3 …* በሕገ ልቦና የሚታወቅ እንደነበር የሚያመለክቱ ናቸው፡፡፣

# <u>አሠርቱ ትእዛዛት</u>

- ለሊቀ ነቢያት ሙሴ የተሰጡት አሠርቱ ትእዛዛት የሚከተሉት ናቸው፡፡
    1. እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ፡፡ ዘጸ 20፡2-3፡፡
    2. የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፡፡ ዘጸ 20፡7፡፡
    3. የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ አክብረውም፡፡ ዘጸ 20፡10፡፡
    4. አባትህንና እናትህን አክብር፡፡ ዘጸ 20፡12፡፡
    5. አትግደል፡፡ ዘጸ 20፡13፡፡
    6. አታመንዝር፡፡ ዘጸ 20፡14፡፡
    7. አትስረቅ፡፡ ዘጸ 20፡15፡፡
    8. በሐሰት አትመስክር፡፡ ዘጸ 20፡ 16፡፡
    9. አትመኝ፡፡ ዘጸ 20፡17፡፡
    10. ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ፡፡ ዘሌ 19፡18፡፡
- አንዳንድ ሊቃውንት ‹‹የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ›› የሚለውን ***<u>ዘጸ 2፡5</u>*** እንደ ሁለተኛ ትእዛዝ በመውሰድ እስከ አትመኝ ድረስ ያለውን አሥር በማድረግ ‹‹ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ›› የሚለውን ***<u>ዘሌዋ 19፡18</u>*** ያስወጡታል፡፡
- ሌሎቹ ሊቃውንት ደግሞ ‹‹የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ›› የሚለው አምልኮን ስለሚመለከትና ‹‹..ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ›› በሚለው ውስጥ ስለሚጠቃለል ለብቻው ሊመዘገብ ኤአገባውም፡፡ ይልቁኑ ጌታችን በሚያስተምርበት ጊዜ ስለትእዛዛት የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ “ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፦ ***<u>ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።</u>*** በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ጸንተዋል።” ***<u>ማቴ 22፡35-40፡፡</u>*** በማለት ፍቅረ ቢጽን እንደ ዋነኛ ትእዛዝ መቁጠሩን ስላመለከተን አሥረኛው ትእዛዝ ***<u>ዘሌ 19፡18</u>*** ነው ይላሉ፡፡

# የመጀመሪያው ትእዛዝ

- “ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።” ***ዘጸ 20፡2-5፡፡***
- አምላካችን እግዚአብሔር ፈጽሞ የሚወደን መሆኑን ‹‹እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ፡፡›› በማለት ገልጾልናል፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች በተለያየ መንገድ ገልጧል፡፡ “ደግሞም፦ እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ።” ዘጸ 3፡6፡፡
- እግዚአብሔር ራሱን ‹‹ ሰማይንና ምድርን የሠራሁ፣ ብርሃንን፡ ሰውን፣ እንስሳትን፡ ዕፅዋትን… የፈጠርሁ እኔ ነኝ›› ወይም ‹‹እኔ ምንም ምን የማይወስነኝ አምላክ ነኝ፣ ከባርነት ያወጣኋችሁ መሆኔን ዘነጋችሁትን?›› በማለት በማስፈራራት የገለጠ አይደለም፡፡
- ነገር ግን ፍቅሩንና ርኅራኄውን በማሳየት እኛም ይህን ለእኛ ያለውን ፍቅሩን፣ ቸርነቱን፣ ርኅራኄውን በተረዳን ጊዜ እንወደውና ፍቅርን ስለ ፍቅሩ እንድንሰጥ በሚያደርግ መልኩ ራሱን ገለጠልን እንጂ፡፡
- እግዚአብሔር ዘወትር ከሚያስደነግጠን ቃል ይልቅ ‹‹እኔ ከተለያዩ ደዌያት የፈወስሁህ፣ በዚህ ዓመት በሕይወትህ የተሳካልህ እንድትሆን የፈቀድሁልህ፣ ከተለያየ ችግር ነጻ ያወጣሁህ፣ ከመከራም ያዳንሁህ፣ በጎውን ሁሉ ያደረግሁልህ አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፡፡›› በማለት ስለ እስፈሪነቱ ሳይሆን ስለ ፍቅሩና ይቅርታው እንዳንረሳው ስለሚሻ አምላክነቱን ገለጠልን፡፡

# የመጀመሪያው ትእዛዝ

- እኛ እግዚአብሔርን የምንሻውን በምንጠይቅበትና የምንሻውንም ከማግኘታችን አስቀድሞ ብናስታውሰውም ከተቀበልን በኋላ እንረሳዋለን፡፡ ስንቸገር እንጠራዋለን ችግራችን ሲፈታ እንረሳዋለን… ሲርበን ሲጠማን እንጠራዋለን ስንጠግብ ስንረካ እንረሳዋለን…
- ይህን ደካማነታችንን ስለሚያውቅ ያደረገልንን የቸርነት ሥራውን ሲነግረን በቀላሉ እናስታውሳለንና ያደረግሁላችሁን እያሰባችሁ አምልኩኝ ለማለት ፍቅሩንም እያሰብን ከፍቅር በመነጨ አምልኮ እንድናመልከው ጭምር አምላካችሁ እኔ ነኝ ብሎ ተናገረን፡፡
- ለእኛ ‹‹ በዘመኔ ሁሉ ቸርነትህን ያደረግህልኝ አምላኬ ሆይ ተናግሬም ሆነ ዘርዝሬ ስለማልጨርሰው ቸርነትህ አመሰግንኻለሁ እገዛልኻለሁም›› ማለታችን ምንኛ በፊቱ ያማረ ነው፡፡ ለጸሎት ቆመን ይህን፣ ያንም አደረግኽልኝ ቸርነትህንም ፈጽሜ አልረሳውም… ዘንግቸው ስለፍቅርህ ብደክም እንኳ ፈጽሜ ስለ ኃጢአቴ በማፈር ንስሐ እገባለሁ እንል ዘንድ ይገባናል፡፡
- እግዚአብሔር ትእዛዛቱን በዚህ መልክ ለእኛ መግለጡ ምንኛ መልካም ነው!
- እግዚአብሔር የፍቅር አምላክነቱን አምነንና አውቀን እንጂ ከፍርሀት የተነሳ እንድናመልከው የሚሻ አይደለም፡፡
- ‹‹እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ የሚለው›› የሚያመለክተው አምልኮን ነው፡፡ ማቴ 4፡10፣ ኢያ 24፡15፡፡
- አምልኮም ዘወትር በእግዚአብሔር ቤት እየተገኙ መጸለይን፣ መጾምን፣ መስገድን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብንና ትርጉም መረዳትን፣ መዘመርን… የሚያካትት ነው፡፡ ይህን የማያደርግ ማንኛውም የሰው ወገን ‹‹እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ›› በሚለው ኃይለ ቃል ይወቀሳል፤ እግዚአብሔር አምላኩ የሆነለት የሚገባውን አምልኮት ሊያቀርብለት ይገባዋልና፡፡

# የመጀመሪያው ትእዛዝ

- ‹‹እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ›› የሚለው የፍቅሩ መግለጫ ኃይለ ቃል ነው፡፡ "ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፡፡" ***ዮሐ 15፡15*** ባሮች ሳይሆን ወዳጆች እንዳለን፣ በጸሎትም ‹‹አባታችን…›› በሉኝ እንዳለ አስቀድሞ ወዶናልና እንወደዋለን፡፡ ***ቀዳ ዮሐ 4፡19፡፡***
- እግዚአብሔር ለሙሴ እንደነገረው ከቀድሞ ጀምሮ ይህን ፍቅር ይሻው ነበር፡፡ "እስራኤል ሆይ፥ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ። " ***ዘዳግ 6፡4-5፡፡***
- እግዚአብሔር ልቦናንና ፍቅርን፣ በልባዊ ፍቅር ላይም የተመሠረተውን እንጂ የታይታ አምልኮትን አይሻም፡፡ ስለዚህም እስራኤላውያንን ስለ ኃጢአታቸው "ጌታም፦ ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፥ በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፥ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና፥ በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ይፈራኛልና፡፡" ***ኢሳ 29፡13***፣ "ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ።" ***ማቴ 15፡8፡፡*** ላይ እንደተገለጸው የወቀሳቸው፡፡
- እንዴት ልናመልከው እንደሚገባ ሲናገርም "ልጄ ሆይ፥ ልብህን ስጠኝ፥ ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ" ምሳ 23፡26 ሲል ገልጧል፡፡
- ስለዚህ ‹‹እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ›› የሚለው የሚለው ለእግዚአብሔር እንድንታዘዝ፣ እንድናመልከውም የሚያደርገንና የሚያበረታታን ሕይወታችንንም እንድንሰጠው የሚያስገነዝበን ነው፡፡
- ከዚህ በማስከተልም ከፍቅር የተነሳ ያደረግሁላችሁን ሁሉ እያሰባችሁ የምታመልኩኝ አምላካችሁ እኔ ነኝና ‹‹ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ…›› አለን፡፡ እነዚህም ሌሎች የተባሉ አማልክት፦ ገንዘብ፣ መልካም ያደረጉልን፣ ዝና፣ መሪዎች ወይም ታላላቆች፣ ዓለምና የዓለም ፍላጎት፣ ራስን ማምለክ፣ ዓለምና መሻቱ፣ ክህደት፣ ሰይጣን … ናቸው፡፡ እነዚህንም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሳምንት በመመልከት የመጀመሪያውን ክፍል ትምህርት እናጠቃልላለን፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

ይቆየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡